# በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን

# የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት መተዳደሪያ ደንብ

## መግቢያ

ሁሉ በአግባብና በሥርዓት ይሁን /1ኛ ቆሮ 14.40/ ተብሎ በሐዋርያው ቅዱስ ጳውሎስ እንደተነገረው ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ሥራና አገልግሎት የሰመረና የተቃና እንዲሆን አገልጋዩንና ተገልጋዩን ደስ እንዲያሰኝ በእግዚአብሔር ዘንድ ተቀባይነት እንዲኖረው አፈጻጸሙ መልካም ሥነ ሥርዓት ሊኖረው ይገባል፡፡ ስለሆነም ለአፈጻጸሙም መመሪያና ደንብ የሚያስፈልገው በመሆኑ፡፡

ቤተ ክርስቲያናችን በቅዱሳት መጻሕፍት በሐዋርያትና በሊቃውንት አበው ቀኖናውያን ሕጎች ላይ የተመሰረተ ሕገ ቤተ ክርስቲያንና አጠቃላይ መመሪያና ደንብ ቃለ ዓዋዲ ያላት በመሆኑ፣

የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በብዙ ገጽታው ከሌሎች አህጉረ ስብከት የተለየ በመሆኑ ይኸውም አዲስ አበባ የሀገሪቱ ርዕሰ ከተማና የልዩ ልዩ ሀገራት ዲ□ሎማቶችና ዓለም አቀፍ ተቋማት መቀመጫ በመሆኗ በዚሁ ሀገረ ስብከት ያሉ ገዳማትና አድበራት አገልግሎት ሰፊ ከመሆኑ ጋር ተያይዞ አገልግሎቱን በተገቢው ሁኔታ ለማዳረስና የአስተዳዳሪዎችና የመደበኛ አገልጋዮች ሹመትና አቀጣጠር፣ ዝውውርና ዕድገት ሹም-ሽርና የሥነ ሥርዓት ውሳኔ መብትና ግዴታ መመሪያን የተከተለ እንዲሆን ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

ከሀገረ ስብከት እስከ አጥቢያ አብያተክርደርቲያናት  የተዘረጋው መዋቅር የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር የቃለ ዐዋዲውን ደንብ የተከተለ የሥራ አፈጻጸም እንዲኖረው ማድረግ አስፈላጊ በመሆኑ፣

የአዲስ አበባ ገዳማትና አድባራት መንፈሳዊ አመራር በይበልጥ የተሟላና የተቃና ቢሆን ለሌሎች አህጉረ ስብከት መልካም ምሳሌ መሆን እንደሚችል በመገንዘብ በቃለ ዐዋዲው የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ደንብ ይዘት የተዘጋጀ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከትን ብቻ የሚመለከት በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፲፺ ን.ቁ ፪ ድንጋጌ መሠረት በ1991 ዓ.ም የወጣው ደንብ ለ፪ኛ ጊዜ ተሻሽሎ ወጥቷል፡፡

## ክፍል አንድ

## ጠቅላላ ድንጋጌዎች

### አንቀጽ ፩

### አጭር ርዕስ

ይህ ደንብ በኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቆ የወጣ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት መተዳደሪያ ደንብ ቁጥር------፳፻፲፩ ዓ.ም ተብሎ ሊጠቀስ ይችላል፡፡

### አንቀጽ ፪

### ትርጓሜ

**፩". ቤተ ክርስቲያን" ማለት፡-** ክርስቶስን በተዋሕዶ አንድ አካል አንድ ባህርይ ብላ የምታምን ሐዋርያዊት፣ ጥንታዊት፣ ታሪካዊትና ብሔራዊት ቤተ ክርስቲያን ማለት ነው፡፡

**፪". ቅዱስ ሲኖዶስ ማለት፡-** ቅዱስ ፓትርያርክ፣ ሊቃነ ጳጳሳትና ኤጲስ ቆጶሳት ያሉበት ዓቢይ ጉባኤ ማለት ነው፣

**፫". ፓትርያርክ"** ማለት፡- የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ርዕሰ አበው አበ ብዙኃን ፤ መሪ ማለት ነው፣

፬". ቋሚ ሲኖዶስ" ማለት፡-

- ሀ. ቅዱስ ፓትርያርክ
- ለ. የቅዱስ ሲኖዶስ ዋና ጸሐፊ
- ሐ. የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጠቅላይ ሥራ አስኪያጅ
- መ. ከሲኖዶስ አባላት መካከል ዐራት ሊቃነ ጳጳሳት ወይም ኤጲስ ቆጶሳት በየሦስት ወሩ እየተመደቡ መደበኛውን የቤተ ክርስቲያኒቱን የዕለት ተዕለት ሥራ የሚፈጽምና የሚቆጣጠር አካል ነው፣

**፭". ሊቀ ጳጳስ ማለት"፡- በሕገ ቤተክርስቲያን ለሊቀ ጳጳስ የተሰጠው ትርጉም እንደተጠበቀ ሆኖ** በቅዱስ ሲኖዶስ የተሰየመ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ነው፣

**፮“. ሀገረ ስብከት” ማለት፡-** የሀገሪቱ /ርዕሰ ከተማ / ማዕከል የሆነ በሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፯ በንዑስ ቁጥር ፫ መሠረት ቅዱስ ሲኖዶስ ባወጣው በዚህ ደንብ የሚተዳደር የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ነው፣

**፯“. ሥራ አስኪጅ” ማለት፡-** ተጠሪነቱ ለሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ የሆነ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ማለት ነው፣

**፰“. የአስተዳደር ጉባኤ” ማለት፡-** በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ እርሱ በሌለ ጊዜ በሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ የሚመራ የክፍል ኃላፊዎች የሚገኙበት ስብሰባ ማለት ነው፣

**፱. “ክፍለ ከተማ ቤተ ክህነት” ማለት፡-** በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በስሩ ያሉ አድባራትና ገዳማት የሚከታተል መዋቅር ነው፣

## <u>አንቀጽ ፫</u>

## <u>የደንቡ አተረጓጎም</u>

፩. ይህ ደንብ ከሕገ ቤተ ክርስቲያንና ከቃለ ዓዋዲ ደንብ ጋር ተጣጥሞ ይተረጎማል፣

፪. የዚህ ደንብ ድንጋጌዎች ያልተሟሉ በሆኑባቸው ጉዳይ ሁሉ እንደ አግባብነቱ በሕገ ቤተ ክርስቲያን እና በቃለ ዓዋዲ ደንብ ድንጋጌዎች ይሸፈናል፣

## <u>አንቀጽ ፬</u>

## <u>ዓላማ</u>

፩. በአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የሚገኙትን ገዳማት፣ አድባራትና ገጠር ነክ አብያተ ክርስቲያናት ለማስተዳደርና ለመቆጣጠር፣ ለማስፋፋትና ለማጠናከር፣

፪. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን እምነትና ቀኖና እንዳይፋለስ ለመጠበቅና ለማስጠበቅ፣

፫. ጥንታዊውን የቤተ ክርስቲያን ትምህርት ለመጠበቅና ለማስፋፋት፣

፬. ስብከተ ወንጌልን፣ ሰበካ ጉባኤያትንና የሰንበት ት/ቤቶችን ለማደራጀት ለማስፋፋትና ለማጠናከር፣

፫. በሀገረ ስብከቱ ገዳማትና አድባራት የሚገኙትን ቅርሶች ለመጠበቅና ለማስጠበቅ እንዲሁም ለጎብኝዎች በሚያመች ሁኔታ ተመዝግበው እንዲጎበኙ ለማድረግ፣

፮. የሀገሪቱ ርዕሰ ከተማ / ማዕከል / እንደመሆኑ በሀገር አቀፍ ደረጃ ከቤተ ክርስቲያኒቱ የሚጠበቅበትን መንፈሳዊ ዓላማና ተግባር ለመፈጸም ነው፣

<u>አንቀጽ ፫</u>

<u>የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሕጋዊ ሰውነት</u>

፩. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በሀገሪቱ የፍትሐ ብሔር ሕግ ቁጥር ፫፻፺፰ እና ፫፻፺፱ በተደነገገው መሠረት ሕጋዊ ሰውነት ያላት የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን አካል ነው። በዚህ መሠረት ውል የመዋዋል፣ የመከሰስና የመክሰስ፣ ሀብት የማፍራት የመቀበልና የማደራጀት መብት አለው፣

፪. ሀገረ ስብከቱ በ፳፻፲፫ ዓ.ም ተሻሽሎ በወጣው ሕገ ቤተ ክርስቲያን በአንቀጽ ፶፮ በንዑስ ቁጥር ፫ በተደነገገው መሠረት በዚህ ልዩ መተዳደሪያ ደንብ ይተዳደራል፣

፫. ሀገረ ስብከቱ በሚያስተዳድራቸው ሠራተኞች ክፍለ ከተሞችና የገዳማትና አድባራት አስተዳደሪዎች ካህናትና ምዕመናን ላይ ባለው የዳኝነት ሥልጣን መሠረት በአስተዳደሩ ሥር ለሚፈጸሙ የሥራ ጉድለቶች በቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግና ሥርዓት መሠረት የመቆጣጠር፣ የመቅጣት፣ የማረም፣ ከሥራ የማሰናበት በጠቅላይ ቤተክህነት በማስጸደቅ በጡረታ የማግለል መብት አለው፣

፬. የሀገረ ስብከቱ ዳኝነት እንደክሱ አቀራረብ እየተመዘነ የሚታየው፡-

ሀ. በዲሲፒሊን ጉባኤ /በሥነ-ሥርዓት ጉባኤ/

ለ. በመንፈሳዊ ፍርድ ቤት

ሐ/ በአስተዳደር ጉባኤ

መ. በጠቅላይ ቤተ ክህነት

ሠ. በቋሚ ሲኖዶስ ይሆናል

፭. እያንዳንዱም የዳኝነት ሥልጣን ከቤተ ክርስቲያኒቱ በወጡና በሚወጡ ሕጎችና ደንቦች መመሪያዎች ይወሰናል፣

## አንቀጽ ፮

## የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት የሥልጣን መዋቅር

ሀ. ቅዱስ ሲኖዶስ

ለ. ቅ□ስ ፓትርያርክ

ሐ. ቋሚ ሲኖዶስ

መ.ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት

ሠ. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ

ረ. የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት

ሰ. የክፍለ ከተማ ቤተ ክህነት

ሸ. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን

## ክፍል ሁለት

## አንቀጽ ፯

## ቅዱስ ሲኖዶስ

ቅዱስ ሲኖዶስ በሕገ ቤተክርስቲያንና በሌሎች የቤተክርስቲያን ሕግጋት ያሉት ስልጣንና ኃላፊነት እንደተተበቀ ሆኖ ፤

፩. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክስ ተዋሕዶ ቤተ ክርስቲያን ቅዱስ ሲኖዶስ የቤተ ክርስቲያኒቱ የመጨረሻው ከፍተኛ የሥልጣን ባለቤት ነው፣

፪. ቅዱስ ሲኖዶስ የሀገረ ስብከቱን ልዩ ልዩ መተዳደሪያ ደንቦችን እንደ አስፈላጊነቱ በየጊዜው ሊያወጣና ሊያሻሽል ይችላል ፣

፫. ቤተ ክርስቲያንን በበላይነት ይመራል ይጠብቃል ፡

## አንቀጽ ፰

## የቅዱስ ፓትርያርኩ ሥልጣንና ተግባር

ቅዱስ ፓትርያርኩ በሕገ ቤተክርስቲያንና በሌሎች የቤተክርስቲያኒቱ ሕግጋት ያሉት ሥልጣንና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ፤

፩. የሀገረ ስብከቱን ገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች ሹመትንና የማዕረግ ስያሜን በተመለከተ በዚህ ደንብ በአንቀጽ ፳፮ በንዑስ ቁጥር ፯ መሠረት ይፈጽማል፣

፪. ስለ ሀገረ ስብከቱ ጉዳይ የመንግስትን ፈቃድ ማግኘት በሚያስፈልግበት ጊዜ ከሀገረ ስብከቱ አቅም በላይ ሲሆን እንደ አስፈላጊነቱ በራሱ፣ በቋሚ ሲኖዶስ ወይም በቅዱስ ሲኖዶስ እያስወሰነ በተግባር ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

፫. ሀገረ ስብከቱን በተመለከተ በቅዱስ ሲኖዶስ ጸድቀው የሚወጡትን ሕግጋት በፊርማው ያስተላልፋል፡፡

## አንቀጽ ፱

## ቋሚ ሲኖዶስ

በ፳፻፲፩ ዓ.ም በወጣው ሕገ ቤተ ክርስቲያን አንቀጽ ፳፰ የተደተደነገገው ተግባርና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ አዲስ አበባ ሀገረ ስብከትን በተመለከተ የሚከተለው ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል ፡-

፩. እንደ አስፈላጊነቱ ከሀገረ ስብከቱ በየጊዜው በጠቅላይ ቤተ ክህነት በኩል የሚቀርበውን የሥራ ሪፖርት እየመረመረ ይወስናል፣ መመሪያም ይሰጣል፣

፪. ከተፈቀደው የሀገረ ስብከቱ ዓመታዊ በጀት ውጭ ክፍያዎች እንዳይፈጸሙ በጠቅላይ ቤተ ክህነት በኩል ይቆጣጠራል፣

፫. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ ለሚካሄዱ የልማት ሥራዎች መመሪያ ይሰጣል፣

፬. . የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎችን ሹመት መርምሮ ያጸድቃል፣

## አንቀጽ ፲

## የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤ

ጠቅላይ ቤተክሕነት በሕገ ቤተክርስቲያንና በሌሎች ሕግጋት የተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ ፤

፩. ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የሥራ አስፈጻሚነትና የአስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው ከፍተኛ አካል እንደመሆኑ መጠን በቅዱስ ሲኖዶስም ሆነ በቋሚ ሲኖዶስ ለሀገረ ስብከቱ የተሰጡትን ደንቦችና መመሪያዎች በትክክል መፈጸማቸውን ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

፪. ከሀገረ ስብከቱ ደረጃ በደረጃ እየተወሰነ የሚቀርብለትን የይግባኝ አቤቱታ እየመረመረ ይወስናል፣

፫. ሀገረ ስብከቱ የሚያቋቁሟቸውን የልማት ተቋማት እንዲሁም ልዩ ልዩ የሕንፃ ሥራ ዕቅዶችን ሀገረ ስብከቱ አጥንቶ ሲያቀርብ እየመረመረ እንደ አስፈላጊነቱ በአስተዳደር ጉባኤ በማስወሰን በሥራ እንዲተረጎሙ ያደርጋል ፤

፬. ለሀገረ ስብከቱና ለክፍለ ከተማ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የሰው ኃይል የሚያስፈልገው ክፍት የሥራ መደብ ኖሮ በእድገትና በዝውውር ወይም በቅጥር መመደብ አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ በሀገረ ስብከቱ በኩል ተከናውኖ ሲቀርብለት መርምሮ ያጸድቃል፣

## ክፍል ሦስት

## አንቀጽ ፲፩

## የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ /ኤጲስ ቆጶስ / ተግባርና ኃላፊነት

የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሊቀ ጳጳስ ኤጲስ ቆጶስ / ተጠሪነቱ ለቅዱስ ሲኖዶስ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፡-

፩. የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በሀገረ ስብከቱ ያለውን ጠቅላላ የቤተ ክርስቲያኒቱን አስተዳደር በበላይነት ይመራል፡

፪. በሀገረ ስብከቱ ለሚገኙት ገዳማት፣ አድባራት፣ ገጠር ነክ አብያተ ክርስቲያናት ካህናትና ምዕመናን መንፈሳዊ አባት እና መሪ ነው፣

፫. የቤተ ክርስቲያናችን ጥንታዊነትና ታሪካዊነት የሀገራችንም ፍቅርና አንድነት በሰላም ተጠብቆ እንዲኖር እንዲሁም የቤተ ክርስቲያናችን እምነት ተከታዮች ሃይማኖታቸውን፣ ሥርዓተ ቤተ ክርስቲያናቸውንና ኦርቶዶክሳዊ ትውፊታቸውን ጠብቀው እንዲኖሩ መንፈሳዊ ጥበቃ ያደርጋል፣

፬. በፍትሕ መንፈሳዊ አንቀጽ ፯ እና ፺ በተደነገገው መሠረት በሥነ ምግባራቸው የተመሰገኑትንና በትምህርት ደረጃቸው ብቁ የሆኑትን እየመረጠ ቀሳውስትንና ዲያቆናትን ይሾማል፣

፭. በዚህ ሕግ አንቀጽ ፷፯ ንዑስ ቁጥር ፯ የተደነገገው እንደተጠበቀ ሆኖ የገዳማትና የአድባራት አስተዳደሪዎችን በዕውቀታቸው በመንፈሳዊ ሕይወታቸው በሙያቸው ብቁ የሆኑትንና በግብረ-ገብነታቸው የታወቁትን እያጠናና እየመረጠ በጠቅላይ ቤተ ክህነት በኩል ለቋሚ ሲኖዶስ አቅርቦ በማስወሰን በፓትርያርኩ ፊርማ ያሾማል፣

፮. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ የሚገኙትን አብያተ ክርስቲያናትን በሚመለከት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ ከሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ ጋር እየመከረ ከመንግሥታውያንና ሕዝባውያን ድርጅቶች ጋር የጽሑፍም ሆነ የቃል ግንኙነት በማድረግ ሥራውን ያከናውናል፣

፯. የሀገረ ስብከቱን አስተዳደር ጉባኤ በሰብሳቢነት ይመራል፣

፰. በትምህርት ችሎታውና በሥራ ልምዱ ብቁ የሆነውን እንዲሁም ሥልጣነ ክህነት ያለውን የሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ከሠራተኛው መካከል በጀት ያለውን መርጦ ለጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ በማቅረብ በቋሚ ሲኖዶስ ሲጸድቅ በጠቅላይ ሥራ አስኪያጁ ፊርማ እንዲሾም ያደርጋል፣

፱. በሀገረ ስብከቱ ስም በባንክ የሚገኘውን ገንዘብ ከሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ጋር በጣምራ ፊርማ ያንቀሳቅሳል፣

<u>አንቀጽ ፲፪</u>

<u>የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት</u>

፩. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ተጠሪነቱ ለመንበረ ፓትርያርክ ጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ነው፣

፪. ሀገረ ስብከቱ በሥሩ በሚተዳደሩት ገዳማት /አድባራትና ገጠር ነክ አብያተ ክርስቲያናት የሥራ አስፈጻሚነትና የአስተዳደር ሥልጣን የተሰጠው ከፍተኛ አካል ነው፣

፫. አዲስ አበባ ሀገረ ስብከት በቅዱስ ሲኖዶስ በተሾመ ሊቀ ጳጳስ ይመራል፣

፬. ሀገረ ስብከቱ ለሊቀ ጳጳሱ ተጠሪ የሆነ አንድ ሥራ አስኪያጅ ይኖረዋል እንደ አስፈላጊነቱም ም/ሥራ አስኪያጅ እና ጸሐፊ ሊመደብለት ይችላል፣

፭. የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ተጠሪነታቸው ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የሆኑ ኃላፊዎች ያሉት ከዚህ በታች የተመለከቱት ዋና ክፍሎች ይኖሩታል፡-

ሀ.የገዳማት አስተዳደር ዋና ክፍል

ለ. የትምህርትና ማሰልጠኛ ዋና ክፍል

ሐ. የስብከተ ወንጌልና ሐዋርያዊ ተልዕኮ መምሪያ ዋና ክፍል

መ. የካህናት አገልግሎት ዋና ክፍል

ሠ. የሰበካ ጉባኤ ማደራጃ ዋና ክፍል

ረ. የሰንበት ት/ቤት ማደራጃ ዋና ክፍል

ሰ. የሕግ አገልግሎት ዋና ክፍል

ሸ. የአስተዳደር ዋና ክፍል

ቀ. የሂሳብና በጀት ዋና ክፍል

በ. የቁጥጥር አገልግሎት ዋና ክፍል

ተ. የዕቅድና ልማት ዋና ክፍል

ቸ. የቅርስ ምዝገባና ጥበቃ ዋና ክፍል

ነ. ጠቅላላ አገልግሎት ዋና ክፍል

ኀ.የሕዝብ ግንኙነት ዋና ክፍል

፮. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ከአጥቢያ እስከ ሀገረ ስብከት የሥራ ክፍሎች ዝርዝር በቃለ ዓዋዲ ደንብ ምዕራፍ ፬ ከአንቀጽ ፲፮ እንዲሁም የሚያከናውናቸው ተግባራት በቃለ ዓዋዲው ደንብ ምዕራፍ ፬ ከአንቀጽ ፲፯-፴ የተዘረዘረው ነው፡፡ በቃለ ዓዋዲው ደንብ ለወረዳ የተሠጠው መዋቅርና የሥራ ክፍፍል ሥልጣንና ኃላፊነት በዚህ ደንብ ለክፍለ ከተማ ተሰጥቷል፡፡

## አንቀጽ ፲፫

## የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ተግባርና ኃላፊነት

በሕገ ቤተክርስቲያን አንቀጽ ፶፫ ለአህጉረ ስብከት የተሰጠው ስልጣንና ኃላፊነት እንደተጠበቀ ሆኖ የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖረዋል፡-

፩. ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የሚተላለፉትን የቅዱስ ሲኖዶስ ውሳኔዎችና ልዩ ልዩ መመሪያዎችን በቤተ ክርስቲያን ሕግጋት መሠረት ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣

፪. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ የሚኙትን ገዳማት፣አድባራትና የገጠር ነክ አብያተ ክርስቲያናት እንዲሁም የቤተ ክርስቲያን ተቋማት፣ የክፍለ ከተማ ቤተ ክህነት ጽ/ቤቶችንና የሀገረ ስብከቱ ልዩ ልዩ የሥራ ዘርፎች በቤተ ክርስቲያን ሕግጋት መሠረት ይመራል፣ ያስተዳድራል፣ ይቆጣጠራል፣

፫. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ የሚገኙ ምዕመናን በተደራጀና በተሟላ ሁኔታ የትምህርተ ወንጌል አገልግሎት እንዲያገኙና ስለ ሃይማኖታቸው በሚገባ እንዲያውቁ፣ በመንፈሳዊ ሕይወት እንዲጸኑና በሥርዓተ ቤተ ክርስቲያን እንዲመሩ ለማድረግ በትኩረት ይሠራል፣ ይከታተላል፣

፬. ሀገረ ስብከቱ ተልዕኮውን ለመፈጸም የሚችልበትን የገቢ ምንጭ ለማስገኘት የሚረዱ የልማት □ሮጀክቶችን እያጠና የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት የሚለማበትን መንገድ ያመቻቻል፣ ሥራውንም በቤተ ክርስቲያን ሕግጋትና ደንቦች መሠረት ይፈጽማል፣

፭. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ የሚንቀሳቀስ ማንኛውም የቤተ ክርስቲያን ሀብትና ንብረት በቤተ ክርስቲያን የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ደንብ መሠረት የሚከናወን መሆኑንና ለቤተ ክርስቲያን አገልግሎት ብቻ መዋሉን ይቆጣጠራል፣

፮. የዓመቱን የሀገረ ስብከቱን የሥራና የአገልግሎት ዕቅድና በጀት በሀገረ ስብከቱ አስተደደር ጉባኤ አስወስኖ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ያቀርባል፣ ሲጸድቅም ተግባራዊ ያደርጋል። በዕቅዱ መሠረት የተከናወነውንም የዕቅድ አፈጻጸም ዘገባ በየዓመቱ ሪፖርት ያደርጋል፣ ጠቅላይ ቤተ ክህነት የማያውቀው እና ያላጸደቀው የሀገረ ስብከቱ ዓመታዊ በጀት የልማት

ፕሮጀክት እና የሰው ኃይል ቅጥር፣ ዝውውርና ዕድገት እንዲሁም የደመወዝ ጭማሪ ሕጋዊነት አይኖረውም፣

፯. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ በሚገኙ ገዳማት፣ አድባራትና የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን የሚገኘውን የሰው ኃይል ቅጥር፣ የሥራ ዝውውር፣ ዕድገት፣ የደመወዝ ጭማሪ፣ የሥነ-ሥርዓትና ሌሎች አስተዳደራዊ ጉዳዮችን በቤተ ክርስቲያን የሰው ሀብት አስተዳደር ደንብ መሠረት ተግባራዊ ያደርጋል፡፡

፰. በየዓመቱና አስፈላጊ ሆኖ በሚገኝበት ጊዜ በሥሩ የሚኙትን ገዳማት፣ አብያተ ክርስቲያናትና የልዩ ልዩ ተቋማት የፋይናንስና የንብረት አያያዝ በሂሳብ አጣሪ /ኦዲት/ እንዲመረመር ያደርጋል፣

፱. በየደረጃው የሚገኙ የቤተ ክርስቲያን አገልጋዮች ስለ ቤተ ክርስቲያን ነባራዊ ሁኔታዎች፣ ስለ መንፈሳዊ አገልግሎታቸውና ስለሚጠበቅባቸው መንፈሳዊ ግዴታ የሚማሩበትና የሚያውቁበት የዕውቀትና የክህሎት ማበልጸጊያ ስልጠናዎችን በየጊዜው እያዘጋጀ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፲. በአብያተ ክርስቲያናት በገዳማትና በአድባራት ዙሪያ የሚገኙ ምዕመናን መንፈሳዊ ደኅንነት እንዲጠበቅ፣ አገልግሎቶች እንዲጠናከሩና የምዕመናን ቁጥር እንዲጨም በትኩረት ይሠራል ሁኔታዎችንም ያመቻቻል፣

፲፩. ከቅዱስ ሲኖዶስና ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት እየተወሰኑ የሚላኩለትን ሌሎች ተግባራትን ያከናውናል፣

፲፪.የሀገረ ስብከቱ ካህናት፣ የአገልጋዮችና የሠራተኞች የገቢ እና የኑሮ ሁኔታ የሚሻሻልበት መንገዶች እያጠና በቤተ ክርስቲያን ሕግ መሠረት ይፈጽማል፡፡

፲፫. ሀገረ ስብከቱ በሥሩ ለሚገኙት የቤተክርስቲያን አስተዳደር ከፍተኛ የሥራ አስፈጻሚና መሪ ነው፤

፲፬. ሀገረ ስብከቱ የአጥቢያ የክፍለ ከተማ ሰበካ ጉባኤ ጽ/ቤት በቃለ ዓዋዲ የተመከተውን በሙሉ እየፈጸመና እያስፈጸመ በተጨማሪ በሥሩ የሚገኙትን የአጥቢያ አብያተ

ክርስቲያናት የዕለት ተዕለት አጠቃላይ መንፈሳዊና ማኅበራዊ አስተዳደራዊ አገልግሎት አፈጻጸም የተሟላ መሆኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣ ያስተባብራል፣

፲፭.የየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የሰበካ ጉባኤ ሥራ አስፈጻሚ ጉባኤ ምርጫን በቃለ ዓዋዲውና በዚህ ደንብ መሠረት ይፈጽማል ያስፈጽማል፣

፲፮.የአገልጋይ ካህናትንና የጽ/ቤት ሠራተኞችን ቅጥርና ዝውውር በሚመለከት በዚህ ደንብና በሕገ ቤተ ክርስቲያንና በቃለ ዓዋዲው የሰበካ መንፈሳዊ ደንብ በተመለከተው መሠረት መፈጸሙን ይከታተላል፣

፲፯.ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን በጉባኤ እየተወሰኑ በይግባኝ የሚቀርቡለትን ጉዳዮች እየተቀበለ በጉባኤ አይቶና አጥንቶ ውሳኔውን በውሳኔ ይሽራል ወይም ያጸድቃል ወይም ለበላይ አካል ያስተላልፋል፣

፲፰.በጉባኤ የተሰጠውን ውሳኔ ለተወሰነለትና ለተወሰነበት በማሳወቅ ውሳኔው በሥራ ላይ እንዲውል ያደርጋል፣

፲፱.በውሳኔው ቅር የተሰኘ ቢኖርና ይግባኝ ሲጠይቅ ሕግ በሚፈቅደው መሠረት ይግባኙን ይሰጣል፣የልማት ዕቅድ እያወጣ ተግባራዊ እንዲሆን ያደርጋል አፈጻጸሙንም ይከታተላል ፤

፳. በሀገረ ስብከቱም ሆነ በገዳማትና አድባራት ልዩ ልዩ የልማት ሥራዎች የሚለሙበትን የልማት ዕቅድ እያወጣ ተግባራዊ እንዲሆኑ ያደርጋል አፈጻጸማቸውንም ይከታተላል ፤

## አንቀጽ ፲፩

## የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ሹመት

**1.** ለሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅነት ዕጩ ሆኖ ሊቀርብ የሚችለው የሚከተሉትን መሥፈርቶች የሚያሟላ መሆን ይኖርበታል፤

ሀ/. ዕድሜው ከ፴--፶ (ከሠላሳ እስከ **ሃምሳ** ) የሆነው፤

ለ/ .ሥልጣነ ክህነት ያለውና ማስተማር የሚችል፤

ሐ./ ከቤተ ክርስቲያን አብነት ት/ቤቶች በአንድ ትምህርት ወይም ከመንፈሳውያን የከፍተኛ የትምህርት ተቋማት ኮሌጆች የተመረቀ፤

መ./ በአስተዳደር ሙያ ቢያንስ የመጀመሪያ ዲግሪ ያለው፤ የተመደበበትን ሀገረ ስብከት መምራት የሚያስችል ችሎታ ያለው ፤

ሰ/. በሀገረ ስብከት ስራ አስኪያጅነት ቢሾም የሚፈጽማቸውን አንኳር ተግባራት የሚያሳይ ምክረ ሀሳብ ማቅረብ የሚችል ፤

ረ. የሚመረጠው ሥራ አስኪያጅ ከሀገረ ስብከቱ ሠራተኞች መካከል ሆኖ ለቦታው በጀት ያለው ነው፡፡

**2.** የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ በሥራ አፈጻጸም ብቃት፣ በአገልግሎትና በእድገት ካልሆነ በቀር ወደ ጠቅላይ ቤተ ክህነት አይዛወርም፡፡ በተመደበበት የሥራ አስኪያጅነት የሥራ መደብ መቀጠል የማይችል ሆኖ የዲሲፒሊን ጉድለት ከሌለበት ደረጃው ተጠብቆ በሀገረ ስብከቱ በሌላ የሥራ መደብ እንዲሠራ ይደረጋል፣

## አንቀጽ ፲፩

## የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ተግባርና ኃላፊነት

**የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ሥራ አስኪያጅ ተጠሪነቱ ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሆኖ የሚከተሉት ተግባርና ኃላፊነት ይኖሩታል፣**

**፩. በሀገረ ስብከቱ ዓመታዊ የድርጊት መርሐ-ግብር መሠረት የትምህርተ ወንጌል ሥርጭት የሚስፋፋበትን ምቹ ሁኔታ ይፈጥራል፣**

**፪. በሀገረ ስብከቱ በሚገኙ ክፍለ ከተማዎች የስብከተ ወንጌል አገልግሎት በአግባቡ እንዲዳረስ ተገቢውን ክትትል ያደርጋል፣ ያስተምራል፣**

**፫. በሀገረ ስብከቱ የሚገኙ የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች እንዲሁም የክፍላተ ከተማ ቤተ ክህነት ሥራ አስኪያጆች በልዩ ልዩ የቤተ ክርስቲያን አስተዳደር ጉዳዮች ላይ ትምህርትና**

ስልጠና እንዲያገኙ ያደርጋል፣ የሥልጠናውንም ሂደት እየተገኘ ይገመግማል፣ ይቆጣጠራል፣

፬. በሀገረ ስብከቱ ውስጥ በሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት ውስጥ የአብነት ት/ቤቶች እንዲጠናከሩና በሌለባቸውም እንዲቋቋሙ ይሠራል፣ ክትትልም ያደርጋል፣

፭. በሀገረ ስብከቱ የካህናት ማሠልጠኛ እንዲቋቋም ያደርጋል፣ ማሰልጠኛውም የቤተ ክርስቲያንን ችግር የሚፈቱ ካህናትን የሚያፈራ እንዲሆን ይሠራል፣ ክትትልም ያደርጋል፣

፮. በየጊዜው በቅዱስ ሲኖዶስ የሚወሰኑት መመሪያዎችና ከጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የሚተላለፉት ትእዛዞች ሁሉ ይፈጽማል፣ ያስፈጽማል፣

፯. የሀገረ ስብከቱን የሰበካ ጉባኤ /ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ/ በሰብሳቢነት ይመራል፣

፰. የሀገረ ስብከቱን ገንዘብና ንብረት ከሊቀ ጳጳሱ መመሪያ እየተቀበለ ያንቀሳቅሳል፣

፱. የሀገረ ስብከቱን የሚንቀሳቀሱና የማይንቀሳቀሱ ንብረቶች በቤተ ክርስቲያን የንብረት አስተዳደር ደንብ መሠረት ያስተዳድራል፣ ይጠብቃል ያስጠብቃል፣

፲. የሀገረ ስብከቱን ዓመታዊ የሥራ እቅድና ለሀገረ ስብከቱ ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ/ ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ/ ያቀርባል፡፡ ሲጸድቅም ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በማሳወቅ ተግባራዊ ያደርጋል፣

፲፩. የዕቅድ አፈጻጸም ዘገባን በየሦስት ወሩ ለሀገረ ስብከቱ ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ/ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ/ ያቀርባል፣

፲፪. በቤተ ክርስቲያን የሰው ኃይል አስተዳደር ደንብ መሠረት የሀገረ ስብከቱን ጽ/ቤት ሠራተኞች ያስተዳድራል፡፡ ከሊቀ ጳጳሱ መመሪያ እየተቀበለ የሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት ሠራተኞችን የመቅጠር፣ የማዛወር፣ በጠቅላይ ቤተ ክህነት በማጸደቅ የደመወዝ መጨመርና ሠራተኛ ማሰናበትን የመሳሰሉት ተግባራት ይፈጽማል፣

፲፫. የሀገረ ስብከት የሰበካ መንፈሳዊ ጉባኤና የሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ ውሳኔዎች ለክፍላተ ከተማ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በማስተላለፍ በየደረጃው ለሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የሰበካ መንፈሳውያን ጉባኤያት እንዲደርሱ ያደርጋል፣ አፈጻጸማቸውን ይከታተላል፣

፲፬. ማንኛውም የሀገረ ስብከቱ ወጭና ገቢ በቤተ ክርስቲያን የፋይናንስና የንብረት አስተዳደር ደንብ መመሪያ መሠረት መከናወኑን ይከታተላል፣ ይቆጣጠራል፣

፲፭. የሀገረ ስብከቱን የሥራ ክፍሎች የዕቅድ አፈጻጸም እየገመገመ ለሀገረ ስብከቱ ሰበካ አስተዳደር ጉባኤ /ሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ/ ዘገባ ያቀርባል፣

፲፮. በሀገረ ስብከቱ የሚገኙ አብያተ ክርስቲያናት የሥራ እንቅስቃሴ በክፍላተ ከተማ ቤተ ክህነት ጽ/ቤቶች አማካኝነት ይከታተላል ይቆጣጠራል፣

፲፯. በሁሉም መስክ የቤተ ክርስቲያን ልዩ ልዩ የመረጃ ቅንብር /ስታቲስቲካዊ/ መረጃ ተጠናክሮና ተመዘግቦ እንዲገኝ የሚመለከተውን የሥራ ክፍል በማገዝ ይሠራል፣

፲፰. ከሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የሚሰጡትን ተጨማሪ ሥራዎች ያከናውናል።

## አንቀጽ ፲፮

## ምክትል ሥራ አስኪያጅ

፩. ምክትል ሥራ አስኪያጁ የሥራ አስኪያጁ ረዳት ሆኖ ይሠራል

፪. ሥራ አስኪያጁ በማይኖርበት ጊዜ ተክቶ ይሠራል፣

፫. ተጠሪነቱም ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ይሆናል፣

## አንቀጽ ፲፯

## የሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ

፩. በዚህ ደንብ አንቀጽ ፲፪ /፳ መሠረት የዋና ክፍል ኃላፊዎች በአባልነት የሚገኙበት አስተዳደር ነክ ጉዳዮችን ማየትና መወሰን የሚችል ጉባኤ ነው፣

፪. የአስተዳደር ጉባኤው ሰብሳቢ የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ነው። እርሱ በሌለ ጊዜ የሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ተክቶ ይሠራል፣

፫. የአስተዳደር ጉባኤ ዋና ዋና ተግባራት፦

ሀ. በቅዱስ ሲኖዶስ፣ በቋሚ ሲኖዶስ፣ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሚወጡትን ሕግጋት መመሪያዎችና ልዩ ልዩ ውሳኔዎች በሥራ እንዲተረጎሙ ያደርጋል፣

ለ.ከእያንዳንዱ የሥራ ዘርፍ በሚቀርበው ጉዳይ ላይ እየተወያየና የሥራ አፈጻጸም ስልት እያወጣ ይወስናል፣

ሐ. የአስተዳደር ችግሮች ሲፈጠሩ /ሲከሰቱ/ እያስጠና መፍትሔ ይሰጣል፣

መ. ደረጃቸውን ጠብቀው በይግባኝ የሚቀርቡትን ጉዳዮች መርምሮ ይወስናል፣

<u>አንቀጽ ፲፰</u>

<u>የክፍለ ከተማ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት መቋቋም</u>

፩. የክፍለ ከተማ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት በቃለ ዓዋዲው የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ደንብ አንቀጽ ፴፩-፴፯ መሠረት በየጊዜው እንደ አገልግሎቱ ስፋት እየታየ ይቋቋማል፣

፪. በቃለ ዓዋዲው የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ደንብ አንቀጽ ፴፩፡-፴፯ ለወረዳ ቤተ ክህነት የተሰጠው ሥልጣንና ኃላፊነት እንዲሁም አደረጃጀት በዚህ ደንብ ለክፍለ ከተማ ተሰጥቷል።

<u>አንቀጽ ፲፱</u>

<u>የአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን መቋቋም</u>

፩. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ተልዕኮውን በክፍላተ ከተማ ቤተ ክህነት ሥር በተዋቀሩ አጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት ይፈጽማል፣

፪. ሀገረ ስብከቱ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲቋቋም በምእመናንና ካህናት ጥያቄ ሲቀርብና የክፍለ ከተማ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ድጋፍ ሲሰጥ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲቋቋም ፈቃድ ይሰጣል፣

፫. አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እንዲቋቋም ፈቃድ የመስጠት ሥልጣን የሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ነው።

<u>ክፍል አራት</u>

<u>ስለ ቅጥር፣ እድገትና ዝውውር</u>

<u>አንቀጽ ፳</u>

ሀ. <u>የሀገረ ስብከቱ የቅጥር፣ የዕድገትና የዝውውር ኮሚቴ፡-</u>

፩. አዲስ አገልጋይ ካህን ወይም ሠራተኛ ለመቅጠር፣ ዕድገት ለመስጠትና ዝውውርን ለመፈጸም ይቻል ዘንድ ሀገረ ስብከቱ የቅጥር፣ የዕድገትና የዝውውር ኮሚቴ ይኖረዋል፣

፪. የኮሚቴው አባላት ከሀገረ ስብከቱ ሠራተኞች መካከል በችሎታ፣ በታማኝነትና በሥራ ልምድ ብቃት ያላቸው በሥራ አስኪያጅ አቅራቢነት በአስተዳደር ጉባኤ ተመርጠው በሊቀ ጳጳሱ ፊርማ ይመደባሉ፡፡ ቁጥራቸውም ከ፭ ያላነሰ፣ ከ፯ ያልበለጠ ይሆናል፣

፫. ኮሚቴው ከአጥቢያ ቤተ ክርስቲያን እስከ ሀገረ ስብከት ጽ/ቤት ድረስ ባሉ የሥራ ቦታዎች ተመድበው የሚሠሩ ካህናትንና ሠራተኞችን የቅጥር፣ የዕድገትና የዝውውር ጥያቄዎች ሲመሩለት መርምሮ የራሱን ውሳኔ ለሀገረ ስብከቱ ሥራ አስኪያጅ ያቀርባል፡፡ ሥራ አስኪያጁ የቀረበለትን ውሳኔ በአስተዳደር ጉባኤ አስወስኖ ተግባራዊ ያደርጋል፣የሀገረ ስብከትና የክፍለ ከተማ ቤተክህነት ሠራተኛ ሲሆን በጠቅላይ ቤተክህነት አስጸድቆ ተግባራዊ ያደርጋል፤

፬. የኮሚቴው አባላት የሥራ ዘመን ሁለት ዓመት ይሆናል ሆኖም አንድ የኮሚቴ አባል በተከታታይ ለሁለት ጊዜ ብቻ ሊመረጥ ይችላል፡፡

ለ. <u>የኮሚቴው ተግባር፡-</u>

፩. ክፍት የሥራ ቦታ ኖሮ አጥቢያ ቤተ ክርስቲያን፣ ወይም ክፍለ ከተማ ወይም ሀገረ ስብከቱ ሠራተኞች እንዲቀጠርለት ሲጠይቅና ከሥራ አስኪያጅ ሲመራለት ኮሚቴው በቅድሚያ ቅጥሩ የሚያስፈልግ መሆን አለመሆኑን ያጣራል፣

፪. ቅጥሩ አስፈላጊ ሆኖ ከተገኘ በዚህ ደንብ መሠረት ተገቢውን ሥነ-ሥርዓት በመከተል የአመራረጡን ሁኔታ ያከናውናል፡፡

ሐ. <u>ክፍት የሥራ መደብን ስለማሳወቅ፡-</u>

፩. ከ15 ቀን በፊት በአስፈላጊው ቦታ ሁሉ ማስታወቂያ እንዲወጣ ያደርጋል፣

፪. በሚወጣው ማስታወቂያ ላይ፡-

- ክፍት የሥራ መደቡ መጠሪያ
- ተፈላጊው የትምህርት ደረጃና የሥራ ልምድ

- የሥራ ቦታ
- ደመወዝ
- አመልካቾች እንዴት ማመልከት እንደሚችሉና ለማንና የት ማመልከቻቸውን እንደሚሰጡ
- የማመልከቻ መቀበያ ቀን
- የጊዜ ገደቡ
- ሌላም አስፈላጊ መረጃ ቢኖር መግለጽ ይገባል፡፡

፫. ሀገረ ስብከቱ የውስጥም ሆነ የውጭ አመልካቾች የሚያቀርቡትን ማመልከቻ መረጃዎችና ፎቶግራፎች በትክክል መዝግቦ ለቅጥር፣ ዕድገትና ዝውውር ኮሚቴ ያቀርባል፣

መ. <u>የሠራተኛ ቅጥር ምርጫ ሂደት፡-</u>

፩. ኮሚቴው ከሚመለከተው አካል ተዘጋጅቶ የሚቀርብለትን የአመልካቾች ማስረጃ በመመሪያው መሠረት መሟላቱን ካረጋገጠ በኋላ የሥራ መደቡን ጠባይና የተቀጣሪዎችን የአካልና የአእምሮ ጤንነት በመገምገም ተወዳዳሪዎችን የሚመርጥበትን የመመዘኛ ዘዴ ይወስናል፡፡ ይኸውም የገቢር ፈተና፣ የቃል መጠይቅ፣ ወይም ሁለቱንም ሊሆን ይችላል በኮሚቴው አባሎች የተሰጠው ነጥብ የማይቀራረብ ቢሆን ምን መደረግ እንዳለበትና የማለፊያው ነጥብ ስንት መሆን እንዳለበት በቅድሚያ ይወስናል፡፡

፪. ኮሚቴው እንደሁኔታው ከሚመለከተው ባለሥልጣን ጋር በመነጋገር ከመመሪያው ጋር በማይቃረን ሁኔታ የራሱ የሆነ የአሠራር ሥነ-ሥርዓት መመሪያ ይኖረዋል፣

፫. የኮሚቴው የሥራ አፈጻጸም በሙሉ በቃለ ጉባኤ ይመዘገባል፡፡ እንዲሁም የተቀበላቸውንና ያልተቀበላቸውን ተወዳዳሪዎች ስም ከነምክንያቱ በዝርዝር በቃለ ጉባኤው አመልክቶና ተፈራርሞበት የውሳኔ ሃሳቡን ላዘዘው ባለሥልጣን ያቀርባል፡፡

## <u>አንቀጽ ፳፩</u>

## <u>ቅጥርን ስለማሳወቅ</u>

፩.ተቀጣሪው የጤና ምርመራ ውጤት ከታወቀ ሆስፒታል፣ በሥራ ላይ የነበረ ከሆነ ከነበረበት መ/ቤት ወይም ቤተ ክርስቲያን የስንብት ደብዳቤ ሲያቀርብና ስለግለሰቡ አስፈላጊው ማጣሪያ

ከተደረገ በኋላ የቅጥር ደብዳቤ ተዘጋጅቶና በሥራ አስኪያጁ ተፈርሞ እንዲደርሰውና የደብዳቤውም ቅጂዎች ለሚመለከታቸው ክፍሎች እንዲደርሳቸው ይደረጋል፣ለሀገረ ስብከት እና የክፍለ ከተማ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት የሥራ መደብ ሲሆን፣ ቅጥርን ከማሳወቅ በፊት ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ቀርቦ እንዲጸድቅ ይደረጋል፣

፪.የቅጥር ደብዳቤው የሚከተሉትን ነጥቦች የያዘ ይሆናል፡፡

ሀ. የተቀጠረበት የሥራ መደብ

ለ. የተቀጠረበት የሥራ ክፍልና ቦታ

ሐ. ቅጥሩ የሚጸናበት ቀን

መ. የሚከፈለው የደመወዝ ልክ

ሠ. የቅጥሩ የሙከራ ጊዜ

፫. ሠራተኛው ወይም አገልጋዩ በቋሚነት ከመመደቡ በፊት የሶስት ወር የሙከራ ጊዜ ይኖረዋል፡፡ ሠራተኛው ለተመደበበት ሥራ ብቁ ሆኖ ካልተገኘ የሙከራ ጊዜው ከማለቁ በፊት በደብዳቤ እንዲሰናበት ይደረጋል፡፡

<u>አንቀጽ ፳፪</u>

<u>የዕድገት ምደባ</u>

፩. ዕድገት የተጠየቀበት የአድባራት ገዳማትና የአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት የሥራ መደብ በጀት ያልተያዘለት ወይም አዲስ የሥራ መደብ ከሆነ በሀገረ ስብከቱ የአስተዳደር ጉባኤ ተጠንቶ ተግባራዊ ይሆናል፡፡የሀገረ ስብከት እና የክፍለ ከተማ የሥራ መደብ ሲሆን ለጠቅላይ ቤተክህነት በማቅረብ ሲፈቀድ ተግባራዊ ይደረጋል ፤

፪. ክፍት የሥራ መደብ ኖሮ ዕድገት እንዲሰጥ ከሚመለከተው ኃላፊ ሲመራለት የቅጥር፣ የዕድገትና ዝውውር ኮሚቴ የተወዳዳሪዎችን የግል ማኅደርና መረጃዎች መርምሮና አጥንቶ ውጤቱን ከአስተያየት ጋር ለመራለት ባለሥልጣን ያቀርባል፣

፫. ማንኛውም የኮሚቴው አባል ራሱ ወይም ዘመዱ ለዕድገት እጩ ተወዳዳሪ ሆኖ በቀረበበት ጉባኤ በአባልነት አይቀመጥም፣

፬. አንድ ሠራተኛ በትእዛዝ እንዲዛወር ሲደረግ የሠራተኛውን ዕድሜ የትምህርት ደረጃ የሥራ ልምድ፣ የሥራ አፈጻጸም፣ የቤተሰብ ሁኔታ የደመወዝና የመሳሰሉትን በሚገባ ማጤን ያስፈልጋል፣

<u>አንቀጽ ፳፫</u>

<u>የሠራተኛ ዝውውር</u>

<u>በሀገረ ስብከቱ ትእዛዝ ስለሚፈጸም ዝውውር</u>

፩. ሀገረ ስብከቱ አንድን የሥራ መደብ በተፈላጊው የሰው ኃይል ለማሟላት ወይም የባለሙያን እጥረት ለማቃለል፣ ያለውን ትርፍ የሰው ኃይል በማሰማራትና ሥራና ሠራተኛን በማገናኘት ደመወዝ ሳይቀነስ ደረጃው ተተብቆ በተፈቀደው የሰው ኃይል ዕቅድ መሠረት ሠራተኞችን በቋሚነት ወይም በጊዜያዊነት ከአንድ የሥራ ቦታ ወደ ሌላ ለማዘዋወር ይችላል፣

፪. ዝውውሩ የሚፈጸመው በዚህ ደንብ በክፍል አራት በአንቀጽ ፳፩ መሠረት ሲሆን፣ የቦታው በጀት ወይም ደመወዝ ሳይነካ ባለበት ተጠብቆ ነው።

<u>አንቀጽ ፳፬</u>

<u>በሠራተኛው ጥያቄ ስለሚፈጸም ዝውውር</u>

፩. አንድ ሠራተኛ ከአንድ ቤተ ክርስቲያን ወደሌላው ወይም ከአንድ ክፍለ ከተማ ወደ ሌላ ለመዛወር እንዲፈቀድለት ሲጠይቅና ጥያቄው የሚያሳምን ሆኖ ሲገኝ፣ ካለበት ክፍል ለበላይ አካል የድጋፍ ደብዳቤ ሊጻፍለት ይችላል፣

፪. በድጋፍ ደብዳቤው ላይ የሠራተኛው የትምህርት ደረጃ የአገልግሎት ዘመን፣ የሥራ ችሎታና የደመወዝ ልክ፣ ዝውውር የተጠየቀበት ምክንያት ጭምር መዘርዘር ይኖርበታል ስለሆነም ዝውውሩ የሚፈጸመው ሀገረ ስብከቱ በየደረጃው አስጠንቶ ሲያቀርብና የአስተዳደር ጉባኤው ሲያጸድቀው ነው።

፫. ሁለት ሠራተኞች በውዴታ እርስ በእርሳቸው የቦታ ለውጥ ጥያቄ በጽሑፍ ስምምነት ሲያቀርቡ የሁለቱም የትምህርት ደረጃ፣ ሙያ፣ የአገልግሎት ዘመንና የደመወዝ ልክ፣ እንዲሁም የሥራው ጠባይ ተመሳሳይነት ያለው ከሆነና ሁለቱም ሠራተኞች የሚገኙባቸው

የሥራ ኃላፊዎች በዝውውሩ መስማማታቸውን በጽሑፍ ካረጋገጠ ዝውውሩ በአንቀጽ ፳፩ መሠረት በሀገረ ስብከቱ ሊፈቀድላቸው ይችላል፡፡

## አንቀጽ ፳፫
## የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎችን ሹመት

፩. ለገዳም ወይም ለደብር አስተዳደሪነት የሚመረጥ፡-

ሀ. ከቤተ ክርስቲያናችን መደበኛ ትምህርት በአንዱ በመምህርነት የተመረቀ ወይም ተመሳሳይ ችሎታ ያለው ሆኖ የሥራ ልምድ ያለው፣

ለ. በቤተ ክርስቲያናችን የአብነት ትምህርት በቂ ችሎታ ኖሮት

❖ በማሠልጠኛ ተቋማት ገብቶ የተማረና የተመረቀ

፪. የገዳም ወይም የደብር አስተዳደሪነት ሥራ የአስተዳደር ችሎታን የሚጠይቅ ስለሆነ ከላይ ከተገለጹት የትምህርት ችሎታዎች ጋር የአስተዳደር ልምድና ችሎታ እና ስነምግባር ላለው ቅድሚያ ይሰጠዋል፣

፫. የአስተዳደር ልምድና ችሎታ መመዘኛም ከዋና አስተዳዳሪነት በታች ባሉ በአጥቢያ አብያተ ክርስቲያናት በተለያዩ የሥራ ዘርፎች በኃላፊነት ተመድቦ ሲሠራ ባሳየው የሥራ አፈጻጸምና አገልግሎት ይሆናል፣

፬. በንዑስ አንቀጽ ፩ሀ እና ለ የተጠቀሰው ሙያ ኑሮአቸው በቤተ ክርስቲያን መደበኛ አገልግሎት ላይ የተሰየመ ካህናት ከመደበኛ ሥራቸው ጋር ወንጌልን በመስበክና በማስተማር፣

ሀ. ለስብከተ ወንጌል

ለ. ለሰንበት ት/ቤት

ሐ. ለሰበካ ጉባኤ መስፋፋትና መጠናከር

መ. ለካህናት ምዕመናን አንድነት መስፈን በጠቅላላም ለሰበካው ቤተ ክርስቲያን መንፈሳዊና ማኅበራዊ አገልግሎት ተግባራዊ አስተዋጽኦ ያደረጉና ለዚህም ተልዕኳቸው ማስረጃ ያላቸው ካህናት የሥራ ልምድ እንዳላቸው ስለሚቆጠር ለአስተዳዳሪነት እጩ ሆነው ሊቀርቡ ይችላል፣

፫. ሀገረ ስብከቱ ለሹመት ውድድር የሚቀርቡ ዕጩ አስተዳዳሪዎች መጀመሪያ ሲቀጠሩ ያቀረቡትን የሙያ ማስረጃ እንዲሁም ከተቀጠሩ በኋላ በመማር ያሻሻሉትና የደረሱበት የትምህርት ደረጃ ካለ ያበረከቱትን የላቀ የሥራ አስተዋጽኦ ከሚገልጽ ዝርዝር ማስረጃ ጋር የሕይወት ታሪካቸውን በመመርመርና ዕጩዎችንም በግንባር አቅርቦ በማጋነጋገር ለውድድር ብቁዎች ሆነው የሚያገኛቸውን እንዲወዳደሩ ያቀርባል፣

፬. በውድድሩ ተቀራራቢ ውጤት ያገኙ ዕጩዎች ደረጃቸውን የሚመጥን ደብር፣ ገዳም /ቦታ/ እስኪገኝ ስማቸው በተጠባባቂ ዝርዝር ተይዞ ይቆያል፣

፭. የገዳማትና የአድባራት አስተዳዳሪዎች በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ አቅራቢነት ምርጫው በጠቅላይ ቤተ ክህነቱ በኩል ለቋሚ ሲኖዶስ ቀርቦ ሲጸድቅ በቅዱስ ፓትርያርክ ይሾማሉ፣ የማዕረግ ስምም ይሰጣቸዋል፣

፮.በዚህ አንቀጽ ሥር ከተዘረዘረው የገዳማትና አድባራት አስተዳዳሪዎች ሹመትና ምደባ ውጭ የግለሰቦችን ስም እየጠቀሱ ይመደብልን ማለት እና ያለ በቂ ምክንያት እና አስተዳደራዊ ውሳኔ ይነሳልን የሚል ጥያቄ ተቀባይነት የለውም ፤

<u>አንቀጽ ፳፮</u>

<u>ከዝቅተኛ ወደ ከፍተኛ ደረጃ የሥራ ቦታና ደመወዝ ለመዛወር የሚያበቁ ሁኔታዎች</u>

፩. <u>የዕድገት አሰጣጥ ሂደት፡-</u>

ሀ. የአገልግሎት ዘመን

ለ. የሥራ አፈጻጸም

ሐ. ከሥራ ባልደረቦች ጋር ተግባብቶ የመሥራትና የሥነ-ምግባር አቋም

መ. የትምህርት ደረጃ ማለትም፡-

- ለአገልግሎት በደመወዝ ከመመደቡ በፊት የነበረው የትምህርት ደረጃ
- በሥራ ከተመደበ በኋላ ዕውቀትን ለማሻሻል ያደረገው ጥረትና የደረሰበት የትምህርት ደረጃ የመሳሰሉት መመዘኛዎች ናቸው፡፡

፪.በዚህ ደንብ ስለ ቅጥር፣ ዕድገትና ዝውውር ያልተሸፈኑ ድንጋጌዎች በቤተ ክርስቲያኒቱ በጠቅላይ ቤተ ክህነት የሠራተኛ መተዳደሪያ ደንብ እንዲሸፈኑ ይደረጋል።

## አንቀጽ ፳፯

## የዝውውር አፈጻጸም

፩. ማንኛውም የደብር ወይም የገዳም አስተዳዳሪ በተመደበበት ገዳም ወይም ደብር ዝውውር ሲጠይቅና አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ እንዲዛወር ይደረጋል፣

፪. በተመደበበት ደብር ወይም ገዳም የላቀ የሥራ ውጤትና የአመራር ብቃት ያሳየ አስተዳዳሪ የሚዛወረው እንደሥራው ውጤትና የአመራር ብቃት ከፍተኛነት በዕድገት ሊሆን ይችላል፣

፫. ዝውውሩም በሀገረ ስብከቱ ተጠንቶና በአስተዳደር ጉባኤ ታይቶ ሲወሰን ሥራ ላይ ይውላል፣

፬. ማናቸውም ዝውውር ከመፈጸሙ በፊት ሠራተኛው ሥራውንና በእጁ የሚገኘውን ንብረት የሥራ ዕቅድና አፈጻጸም ለማስረከቡ የጽሑፍ ማስረጃ ይሰጠዋል፣

፭. የሠራተኞች ዝውውር በተመሳሳይ ደረጃና ደመወዝ ከክፍል ወደ ክፍል ሲሆን ሊቀ ጳጳሱ አውቆት በሥራ አስኪያጁ ይፈጸማል፣

## ክፍል አምስት

## አንቀጽ ፳፰

## የሠራተኞች መብትና ግዴታ

ሀ. መብት፡-

፩. ለተሾሙበት ደብር የተመደበውን ደመወዝና የቦታው አበል የማግኘት ፤

፪. መጀመሪያ የሥራ መደብ ጥሩ የሥራ ፍሬ ካሳየ ዕድገቱና ዝውውሩ በሀገረ ስብከቱ እየታየ ይፈጸምለታል፣

፫. ሠራተኛው የተመደበበትን ቦታ ደመወዝና ጥቅማ ጥቅም የማግኘት መብት አለው ፤

ለ. ግዴታ፡-

፩. ትምህርተ ወንጌልን በሐዋርያዊ ትውፊት አቀራረብ መስበክ፣

፪. ካህናትንና ምዕመናን ያለአድልዎ በትክክል በሰላምና በፍቅር መምራትና ማስተዳደር

፫. የኢትዮጵያ ኦርቶዶክሳዊ ተዋሕዶ እምነትና ሥርዓት መጠበቅና ማስጠበቅ፣

፬. የሰበካው ምዕመናን ክርስቲያናዊ ግዴታቸውን እንዲያውቁና እንዲፈጽሙ በየጊዜው ተግቶና ነቅቶ መምከርና ማስተማር፣

፭. በጠቅላላ ምዕመናን ከቤተ ክርስቲያኒቱ ሊያገኙት የሚገባቸውን መንፈሳዊና ማኅበራዊ ተልእኮን በምልዐት መፈጸምና ማስፈጸም፣

፮. ከበላይ አካላት የሚተላለፉትን መመሪያዎችና ትእዛዞች ተግባራዊ ማድረግ፣

፯. የቤተ ክርስቲያንን ሀብት፣ ንብረትና ቅርሳ ቅርስ መጠበቅና ማስጠበቅ፣

፰. የቤተ ክርስቲያኑ የገንዘብ ገቢና ወጭ በቃለ ዓዋዲው መመሪያ መሠረት እንዲሠራበት ማድረግ፣

፱.የቤተ ክርስቲያናችን መደበኛ የአብነት ትምህርት መምህራን በደብሩ እንዲመደቡና መደበኛውን የአብነት ትምህርት እንዲያስተምሩ ማድረግ የየደብሩ አስተዳሪዎች ግዴታ ይሆናል፣

፲. የሰንበት ት/ቤትን ማደራጀትና ማጠናከር፣

፲፩. የሰበካውን ክልል ከመናፍቃን ትምህርት መከላከል፣

፲፪.ማዕከላዊ አሠራርን ጠብቆ በመመሪያ መሠረት ለበላይ አካል

## አንቀጽ ፳፱

## ስለ ደመወዝ ጭማሪ

፩. የሚደረገው የደመወዝ ጭማሪም ሆነ ማስተካከያው በቃለ ዓዋዲው መሠረት ቅዱስ ሲኖዶስ ባወጣው የእስኬል መመሪያ መሠረት ይሆናል፣

፪. አንድ ሠራተኛ ከነበረበት ክፍል ወደ ከፍተኛ ደረጃ በዕድገት ሲመደብ ለቦታው የተመደበውን ደመወዝና ሌሎችም ጥቅማ ጥቅሞች ቢኖሩ የማግኘት መብቱ የተጠበቀ ነው፣

፫. እያንዳንዱ ሠራተኛ እንደ የሥራ ቦታው የገቢ አቅም ሁኔታ ታይቶ በየሁለት ዓመቱ የደመወዝ ጭማሪ የማግኘት መብት አለው፣

፬. የአጥቢያ የደመወዝ ጭማሪና ማስተካከያ ተጠንቶ ሲቀርብ በሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤት አስተዳደር ጉባኤ ታይቶ ከጸደቀ በኋላ ተ□ባራዊ □□ረ□ል፣

፭. በጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ሠራተኞች መተዳደሪያ ደንብ አንቀጽ ፲፩ እንደተመለከተው በዲሲፒሊን ምክንያት በሚወሰን ቅጣት የደመወዝ ጭማሪ ለተወሰነ ጊዜ ሊከለከል ይችላል፣

፮. የገንዘብ ወይም የንብረት ጉድለት ላደረሱ ሠራተኞች ያጎደሉትን ገንዘብና ንብረት በሙሉ እስካልተከ ድረስ የደመወዝ ጭማሪ አይሰጣቸውም፣

፯. የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ለሀገረ ስብከቱ ጽ/ቤትና ለክፍለ ከተማ ሠራተኞች የሚሰጠውን ማናቸውንም የደረጃ ዕድገትና የደመወዝ ጭማሪ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት አቅርቦ ያስፈቅዳል፣ሲጸድቅም ተግባራዊ ይደረጋል ፤

፰. የማንኛውም የሥራ መደብ በጀት ይዞት የነበረው ሰው በጡረታ ሲገለል ወይም በሞት ሲለይ ለዚያው የሥራ መደብ ብቁ የሆነ ሠራተኛ ማለት በመምህር በጀት መምህር፣ በአስተዳደር በጀት የአስተዳደር ሠራተኛ ይቀጠራል፣ ወይም በዝውውርና በዕድገት ይመደባል እንጅ ያንዱን ሥራ መደብ በጀት ለሌላ መመደብ የተከለከለ ነው፡፡

## ክፍል ስድስት

## አንቀጽ ፴

## የዲሲፕሊን /ሥነ ሥርዓት/ ኮሚቴ አመሰራረት

፩፥ የዲሲፕሊን /ስነሥርዓት/ ኮሚቴ አባላት በጠቅላይ ቤተክህነት የሠራተኛ አስተዳደር ደንብ አንቀጽ ፲/፫/ መሰረት ከ 4 ያላነሱ ከ 6 ያልበለጡ ሆኖ በአስተዳደር ጉባኤ ተመርጠው በሊቀ ጳጳሱ ይመደባሉ ፤

፪፥ በመስሪያ ቤቱ የተመደበ የቃለ ጉባኤ ጸሐፊ ይኖረዋል ፤

## አንቀጽ ፴፩

## የሥነ ሥርዓት/ ዲሲፒሊን/ አፈጻጸም ሂደት

## በጥፋት ምክንያት በሠራተኛ ላይ ስለሚወሰድ የሥነ ሥርዓት ውሳኔ

### የሥነ ሥርዓት ቅጣት መሠረታዊ ዓላማ፡-

፩. ማንኛውም የሀገረ ስብከቱን ሠራተኛ ለማረምና ለማስተማር፤ አስፈላጊ በሚሆንበት ጊዜም ስራው እንዳይበደል ተገቢውን እርምጃ ለመውሰድ፤

፪. የሠራተኛውን መብት ለማክበርና ግዴታውን ለማሳወቅ፤

፫. ለቀልጣፋ መንፈሳዊ አገልግሎት እና ስራ፣ የቤተ ክርስቲያኗን አሠራር ለማጎልበት፤ አስፈላጊ የሆነውን የሥራ ዲሲፕሊን ለማስከበር፣

፬. የሚወሰደው የስነ ሰርዓት እርምጃ ከተፈጸመው ጥፋት ጋር ተመጣጣኝ እንዲሆን ለማድረግ እንዲያስችል፤

፭. አንድ ሠራተኛ ስራውን በአግባቡ ባለመፈጸሙ ወይም ማድረግ የማይገባውን በማድረጉ ስለ ጥፋቱ ሕግ በሚፈቅደው ዓይነት ተጠያቂነቱ እንደተጠበቀ ሆኖ በዚህ ደንብ መሰረት ለስነ ስርዓት ጉድለት አስተዳደራዊ የቅጣት ውሳኔ ይወሰንበታል፡፡

## ሀ. <u>የቅጣት አይነቶች</u>

ሠራተኛው ማንኛውንም ጥፋት መፈፀሙ ሲረጋገጥ የጥፋቱ ዓይነትና ክብደት ተመዝኖ የሚከተሉት ቀላልና ከባድ ቅጣቶች በአጥፊው ላይ ሊወሰድ ይችላል፡፡

፩. የቃል ማስጠንቀቂያ ወይም ተግሳጽ፣

፪. የፅሁፍ ማስጠንቀቂያ፣

፫. ከ 10 ቀን ያልበለጠ የደመወዝ ቅጣት፣

፬. ከአንድ ወር ያልበለጠ የደመወዝ ቅጣት፣

፭. ያለደመወዝ ከሥራ አ□ልሎ እስከ ሁለት ወር ማቆየት፤

፮. ከስራ መደብና ከደመወዝ እንደጥፋቱ መጠን እና ልክ ከደረጃ ዝቅ ማድረግ፡፡

፯. ከሥራ ማሰናበት፣

## ለ. <u>የቅጣት አፈጻጸም</u>

### <u>ከሥራ ስለማገድ</u>

አንድ ሠራተኛ ጥፋት ፈጽሟል ተብሎ ሲገመት እንደነገሩ ሁኔታ አግባብ ባለው የበላይ አለቃ ከመደበኛ ሥራው የሚታገደው በሚከተሉት ምክንያቶች ነው፡-

፩. ፈጽሟል ከተባለው ጥፋት ጋር አግባብ ያላቸው ማስረጃዎችን በማበላሸት ወይም በመደበቅ ምርመራውን የሚያሰናክል ሆኖ ሲገመት፣

፪. ፈጽሟል የተባለውን ጥፋት ከባድ ከመሆኑ የተነሳ የሌሎች ሠራተኞች ሞራል የሚነካ ወይም በሌሎች ሠራተኞች ላይ ሊኖረው የሚገባውን እምነት የሚያዛባ ሆኖ ሲገኝ፣

፫. ፈጽሟል የተባለውን ጥፋት ከሥራ የሚያስወጣ ወይም ከደረጃ ዝቅ የሚያደርግ ሆኖ ሲገመት፣

፬. በቤተ ክርስቲያኗ ንብረት ላይ ጉዳት ያደርሳል ተብሎ ሲጠረጠር፣

፭. ፈጽሟል ተብሎ የተጠረጠረበትን ጥፋት ሠራተኛው በስራ ላይ ሆኖ ማጣራት የማይቻል እና ጥፋቱን ማጣራት አስፈላጊ ሆኖ ሲገኝ፣

፯. ከዚህ በላይ በተጠቀሱት ምክንያቶች ከሥራ የታገደ የሠራተኛ ጉዳይ በቤተ ክርስቲያኗ በተቋቋመው የሥነ ምግባር ኮሚቴ ተጠንቶ ሲቀርብ ወይም በሚመለከተው ሀላፊ ተጠንቶ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

## ሐ. <u>የዕገዳ አፈፃፀም</u>

፩. ከስራ ታግዶ የሚቆይ ሠራተኛ የታገደበት ምክንያት በጽሁፍ ይገለጽለታል፡፡

፪. የማገጃውን ትዕዛዝ ለሠራተኛው መስጠት ካልተቻለ ግን መታገዱንና የታገደበትን ምክንያት ቀርቦ ለመረዳት የሚችል መሆኑን የሚገልፅ ጽሑፍ በቤተ ክርስቲያኗ ማስታወቂያ ሰሌዳ እንዲለጠፍ ይደረጋል፡፡

፫. ሠራተኛው ከሥራ መታገዱ የሚፀናው የማገጃው ትዕዛዝ ለሠራተኛው ከተሰጠበት ቀን ወይም በማስታወቂያ ሰሌዳው ላይ ከተለጠፈበት ቀን ማግስት ጀምሮ ነው፡፡

፬. ተጠሪነታቸው ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ የሆኑት የገዳም ወይም የደብር አስተዳዳሪዎች እገዳ ተፈፃሚ የሚሆነው በሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ ሲጸድቅ ይሆናል፡፡

## መ. <u>የዕገዳ ጊዜ ገደብ</u>

፩. ሠራተኛው ከሥራ ታግዶ እንዲቆይ የሚደረገው ከሁለት ወር ላልበለጠ ጊዜ ነው፡፡

፪. በዚሁ አንቀፅ ንዑስ አንቀፅ ሀ ተራ ቁጥር ፫ በተገለጸው መሰረት የተፈፀመው እገዳ በተሰጠው የሁለት ወር ጊዜ ገደብ ውስጥ መርምሮም ሆነ አስመርምሮ ውሳኔ ለመስጠት የሚያስችል ከአቅም በላይ የሆነ ምክንያት ካጋጠመው የበላይ አለቃው ይህንን እንደየቅደም ተከተላቸው ለሰበካ ጉባዔው ወይም ለሀገረ ስብከቱ ሊቀ ጳጳስ በማቅረብ የዕገዳውን ጊዜ ለተጨማሪ አንድ ወር ጊዜ አስፈቅዶ ሊያራዝም ይችላል፡፡

፫. ሠራተኛው በተሰጠው ጊዜ ውስጥ ከምርመራ አንጻር የሚፈለግበትን ግዴታ ማሟላትና ግዴታዎችን ማቅረብ አለበት፡፡ ከአቅም በላይ በሆነ ምክንያት ለማቅረብ ካልቻለ ከላይ በተራ ቁጥር ፩ እና ፪ የተሰጠው ጊዜ ካለቀበት ቀን ጀምሮ እስከ አንድ ወር ድረስ ጊዜ ይሰጠዋል፡፡ ከዚህ በኋላ በተገኘው መረጃ ውሳኔ ይሰጥበታል፡፡

## ሠ. እገዳና የደሞዝ ክፍያ

፩. ሠራተኛው ከሥራ ታግዶ እስከ ቆየበት ጊዜ ደመወዙ ታግዶ ይቆያል፡፡

፪. ምርመራው ተጠናቆ ሠራተኛው ፈፅሚል ከተባለው ጥፋት ነፃ ሆኖ ከተገኘ በዕገዳው ጊዜ ያልተከፈለው ደመወዝ ያለወለድ ይከፈለዋል፡፡

፫. የደመወዝ ቅጣትን በሚመለከት የተሰጠ ውሳኔ ካለ እንደተጠበቀ ሆኖ በሠራተኛው ላይ የሚሰጥ ውሳኔ የሥራ ስንብት የማያስከትል ሆኖ ሲገኝ በዕገዳው ጊዜ የተያዘበት ደመወዝ ያለወለድ ይከፈለዋል፡፡

፬. ሠራተኛው የተወሰነበት ቅጣት የሥራ ስንብት ከሆነ ከእገዳው ጊዜ ጀምሮ የተያዘበት ደሞዝ አይመለስለትም፡፡

፭. በሠራተኛው ላይ የተወሰነው ቅጣት ተፈፃሚ የሚሆነው ሠራተኛው ከታገደበት ቀን ጀምሮ ይሆናል፡፡

## ረ. በመንፈሳዊ አስተዳደር ችሎታ እና ዕውቀት ማነስ ስለሚወሰድ የሥነ ሥርዓት ውሳኔ

፩. የገዳሙ ወይም የደብሩ አስተዳደር የመንፈሳዊ አባት እና መሪነት የአስተዳደር ብቃት የሥራ አፈፃፀም ምዘና ከሚጠበቀው በታች ሆኖ ሲገኝ ድክመት ያሳየባቸው ነጥቦች ተጠቅሰው እንዲያሻሻል በጽሑፍ በደረሰው በሶስት ወር ጊዜ ውስጥ ማሻሻል ይኖርበታል፡፡

፪. የአስተዳደር ዕውቀት እና ልምድ እያለው በቸልተኝነት ምክንያት ተገቢውን ደረጃ የጠበቀ የሥራ ውጤት የማይሰጥ መሆኑ ሲረጋገጥ ወይም የሥራ አፈጻጸሙ ሊሻሻል የማይችል ሆኖ ከተገኘ እንደሁኔታው ከደረጃ ዝቅ ብሎ ደመወዙ በተመደበበት ቦታ የሥራ ደረጃ መሰረት እንዲስተካከል ይደረጋል፡፡ የደመወዝ ቅነሳውም በዚሁ ደንብ እና በሠራተኛ መተዳደርያ ደንብ ላይ በተመለከተው መሰረት ይሆናል፡፡

## ሰ. የሥነ ሥርዓት ውሳኔ የሚሰጥባቸውቸው የጥፋት አይነቶች

ከዚህ በታች የተዘረዘሩት ጥፋቶች የሥነ ሥርዓት ቅጣት የሚያስወስዱ ይሆናሉ፡፡

**፩.ቀላል ጥፋቶች**

**የሚከተሉት ድርጊቶች እንደቀላል ጥፋት ይቆጠራሉ፡-**

፩.፩. የቅርብ የሥራ ኃለፊውን ፈቃድ ሳያገኝ ለተወሰነ ጊዜ ከተመደበበት □ሥራ ገበታ መቅረት፤

፩.፪. ከሥራ ኃላፊው የተሰጠውን ሥራዎች በወቅቱ አከናውኖ አለመገኘት ፤

፩.፫. በሥራ ሰዓት የግል ሥራ መሥራት፤

፩.፬. የቤተ ክርስቲያኒቱን ንብረት ያለፈቃድ ለግል ጥቅም መገልገል፤

፩.፭. በሥራ ክፍሉ ውስጥ የሚከሰቱትን ችግሮች በወቅቱ አለመፍታት፤ከአቅም በላይ ሆኖ ሲገኝም በወቅቱ ለሚመለከተው አለማሳወቅ፤

፩.፮. በኃላፊነት የተረከባቸውን ንብረቶች በጥንቃቄ አለመያዝ፤

፩.፯. ኃላፊነትን በመዘንጋት ሥራን መበደልና በሥራ ሰዓት ቸልተኝነት ማሳየት፤

፩.፰. ክብደቱ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይነት ያላቸው ሌሎች የዲሲፕሊን /የሥነ ሥርዓት/ ጥፋቶችን መፈፀም፤ ጥፋቱም በማስረጃ ሲረጋገጥ እንደሁኔታው እየታየ በዚህ አንቀፅ ንዑስ አንቀጽ ሀ ከተራ ቁጥር ፩ እስከ ተራ ቁጥር ፯ ከተዘረዘሩት አንዱ ሊወሰንበት ይችላል።

2. <u>**ከባድ ጥፋቶች**</u>

፪.፩ በቤተ ክርስቲያኒቱ አርማና ማህተም በሀሰት መጠቀም፤

፪.፪ መንፈሳዊ አገልግሎቶች በአግባቡ እንዳይከናወኑ እና ሥራ እንዳይሠራ ሆን ብሎ ማወክ ወይም ከሚያውኩት ጋር መተባበር፤

፪.፫ የበላይ ኃላፊን ወይም ሠራተኛን መዝለፍ ወይም በሥራ ላይ ድብደባ ማካሄድ፤

፪.፬ በመጠጥ ስካር ወይም በሚያሰክሩ እፆች ሱስ ተመርዞ በሥራ ላይ መገኘት፣ ወይም በሥራ ላይ በደል መፈፀም፤

፪.፭ መደለያ፣ ማማለጃ ወይም ጉቦ መቀበል፣

፪.፮ በቤተ ክርስቲኒቱ ቅጥር ግቢ አጸያፊ ድርጊት መፈፀም፤

፪.፯ የቤተ ክርስቲያኒቱን ንብረት ወስዶ / ሰርቆ / ለግል ጥቅሙ አውሎ መገኘት፤ ወይም በሌሎች ሲሰረቅ  ተባባሪ መሆን ወይም ጥፋትን እያዩ በዝምታ ማለፍ፤

፪.፰ ሥራውን ምክንያት በማድረግ ለራስ ወይም ለሌላ ወገን የማይገባ ጥቅም ማስገኘት ወይም ለማግኘትና ለማስገኘት መሞከር፤

፪.፱ ሰነዶችንና መዛግብትን መደለዝ፣መሰረዝ፣ መሰወር፣ ወይም ለሌላ አሳልፎ መስጠት ወይም በሀሰት የገንዘብ ሰነዶችን ማቅረብ፤

፪.፲ ስልጣን ካለው የቤተ ክርስቲያኒቱ ኃላፊ ፈቃድ ሳያገኝ የቤተ ክርስቲያኒቱን መኪና ማሽከርከር ወይም የሚያሽከረክረው መኪና ላይ የደረሰውን አደጋ በመደበቅ ቤተ ክርስቲያኒቱ እንዳታውቀው ማድረግ፤

፪.፲፩ በአንድ ዓመት ጊዜ ውስጥ ተደምሮ ለሰላሳ ቀናት ወይም ለተከታታይ ፭ ቀናት ያለፈቃድ ወይም ያለበቂ ምክንያት ከሥራ መቅረት፤

፪.፲፪ በሥራው አማካኝነት ያገኘውን ወይም የተገለፀውን የቤተ ክርስቲያኒቱን የሥራ ምስጢር ማባከን፤

፪.፲፫ የተሰጠውን የስራ መመሪያ በእምቢተኝነት ባለመቀበል ምክንያት ወይም ከመመሪያ ውጪ በመስራት በስራ ላይ በደል ማድረስ ወይም መጥፎ ውጤት እንዲደርስ ማድረግ፤

፪.፲፬ ቀላል ጥፋቶችን በተደጋጋሚ የፈፀመና በማስረጃ የተረጋገጠበት፤

፪.፲፭ሕጋዊ ባልሆኑ ማሕተሚችና ማስረጃዎች አስመስሎ መጠቀም ፤

፪.፲፮ ክብደቱ ከዚህ በላይ ከተዘረዘሩት ጋር ተመሳሳይ የሆኑ ሌሎች የዲሲፕሊን ጥፋቶችን የፈፀመ ሠራተኛ ከዚህ አንቀጽ ንዑስ አንቀጽ ፪ ከተራ ቁጥር ፪.፩ እስከ ፪.፲፮ ከተጠቀሱት የስነ ስርዓት ውሳኔዎች አንዱ ሊወሰድበት ይችላል፡፡  በተጨማሪም ላጠፋው ጥፋት በሕግ ይጠየቃል፡፡

<u>የዲሲፒሊን ኮሚቴ አወቃቀር፡-</u>

፩. በዚህ ደንብ እና በሌሎች የቤተ ክርስቲያኒቱ ሕግጋት የተጠቀሱትን ግዴታዎች ጥሶ የተገኘ ሠራተኛ ጉዳዩን በሠራተኛ አስተዳደር መተዳደሪያ ደንብ ላይ በተገለጸው አግባብ በሚሰየሙ የድስፕሊን ኮሚቴዎች ጉዳዩ የሚታይ፤የሚመረመር እና የሚወሰን ይሆናል፤

፪. የዲሲፒሊን ውሳኔው ላይ ቅሬታ ያለው ወገን ቅሬታውን በሰበካ መንፈሳዊ ጉባዔ ደንብ ቃለ ዐዋዲ መሰረት ስልጣን ባለው አካል ዘንድ መዋቅሩን ተከትሎ ይግባኝ የማቅረብ መብቱ የተጠበቀ ነው፡፡

፫. ይህን ደንብ እና ቃለ ዓዋዲውን የሰበካ መንፈሳዊ ደንብ እንዲሁም የቤተ ክርስያኒቱን የሠራተኛ መተዳደሪያ ደንብ እና ሕገ ቤተ ክርስቲያን በሚተላለፍ ላይ የሚሰጠው ውሳኔ ከዚህ ደንብ በተጨማሪ በሠራተኛ መተዳደሪያ ደንብ እና በቃለ ዓዋዲው አንቀጽ 63 መሠረት ይፈጸማል፡፡

<u>ክፍል ሰባት</u>

<u>አንቀጽ ፴፪</u>

<u>በጀትን በተመለከተ</u>

፩.የየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን ዓመታዊ የካፒታልና የመደበኛ በጀት ድልድል የበጀት ዓመቱ ከመድረሱ በፊት በሰበካ ጉባኤው ተጠንቶና ተበጅቶ በክፍለ ከተማ ቤተ ክህነት በኩል ለሀገረ ስብከቱ ይቀርባል፣ ሀገረ ስብከቱም የቀረበለትን በጀት በአስተዳደር ጉባኤው መርምሮ ያጸድቃል፣

፪.የአዲስ አበባ ሀገረ ስብከት ዓመታዊ በጀት በቃለ ዓዋዲው ደንብና በፋይናንስ አሠራር መሠረት ለሀገረ ስብከቱ አስተዳደር ጉባኤ አቅርቦ ሲስማማበት ከአስተያየት ጋር ለጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤት ይልካል፣

፫.የጠቅላይ ቤተ ክህነት ጽ/ቤትም ከሀገረ ስብከቱ የተላለፈለትን በጀት መርምሮ በማስጸደቅ በሥራ ላይ እንዲውል ለሀገረ ስብከት ያስተላልፋል፣

፬.በክፍለ ከተማና በሀገረ ስብከት ደረጃ ከተፈቀደው በጀት ውጭ ለአንዳንድ አስቸኳይ ጉዳዮች የገንዘብ ወጭ ሲያስፈልግ እንደ ጉዳዩ አስቸኳይነት ቅደም ተከተል በመስጠት የተጠየቀው

ወጭ በጠቅላይ ቤተ ክህነት ሲፈቀድና ሲጸድቅ በሥራ ላይ ይውላል፣በጠቅለቀይ ቤተክህነት ሳይጸድቅ ከበጀት ውጭ የትኛውም ዓይነት ወጪ ተግባራዊ አይደረግም ፤

፰.ሀገረ ስብከቱ ከገዳማትና አድባራት ከሰበሰበው ዓመታዊ የፐርሰንት ገቢ ለጠቅላይ ቤተ ክህነት በቃለአዋዲው የሰበካ መንፈሳዊ አስተዳደር ደንብ መሰረት ገቢ ያደርጋል ፡፡

<u>አንቀጽ ፴፫</u>

<u>ቁጥጥርን በተመለከተ</u>

፩. ሀገረ ስብከቱ በቃለ ዓዋዲው አንቀጽ ፳፯ መሠረት በየአጥቢያ ቤተ ክርስቲያኑ ያለው የቁጥጥር ሥራ ተጠናክሮ በየአጥቢያው ቤተ ክርስቲያን የሚገኙት የስዕለትና የሙዳየ ምፅዋት ሣጥኖች ምልክትና መለያ ቁጥር እየተሰጣቸው ብዛታቸው የታወቀና የተቀመጡበት ቦታ በግልጽና አስተማማኝ መሆኑን ያረጋግጣል፣ ያልተመዘገቡና ያልታወቁ ሣጥኖችም ሆነ ሌሎች የገንዘብ መሰብሰቢያዎች ሁሉ በቅጽረ ቤተ ክርስቲያን ውስጥ ያለመኖራቸውን በጥብቅ ይቆጣጠራል፣

፪. የስዕለትና የሙዳየ ምፅዋት ሣጥኖች በሥራ ላይ ከመዋላቸው በፊት በሥራ አስፈጻሚ ኮሚቴ በተመረጡ አባላት፣ አስተዳዳሪው፣ ሂሳብ ሹሙ፣ ተቆጣጣሪው የሀገረ ስብከት /የክፍለ ከተማ ተወካይ/ በሚገኙበት የጋራ ፊርማ መታሸጋቸውንና ሲከፈቱም የፈረሙት አባላት ሁሉ መገኘታቸውን ይከታተላል፣

፫. በዓውደ ምሕረቱም ሆነ በሌላ ቦታ ሙዳየ ምጽዋትና ጥላ በማዞር ስጋጃ በማንጠፍ ወይም በሌላ መንገድ የሚሰበሰበው ማናቸውም ገንዘብ ልዩ ልዩ ስጦታ ሁሉ በአግባቡ እየተመዘገበ በቤተ ክርስቲያኑ ሕጋዊ ካርኒ /ደረሰኝ/ ገቢ መሆኑን ያረጋግጣል፣

፬. በስዕለትና በሌላም ምክንያት ለቤተ ክርስቲያን የሚሰጡት እንስሳት፣ ብርና ወርቅ እንዲሁም ልዩ ልዩ ንብረቶች ሁሉ ግምታቸው እንዲታወቅና በሕጋዊ መንገድ ገቢ እንዲሆኑ አስፈላጊውን ሁሉ ያደርጋል፡፡

፭. የሀገረ ስብከቱን የንዘብና የንብረት እንቅስቃሴ በየዓመቱ በበጀት ዓመቱ መዝጊያና አስፈላጊ በሆነ ጊዜ ሁሉ ጠቅላይ ቤተ ክህነቱ ወይም ቋሚ ሲኖዶሱ እንዲመረመር ያደርጋል፣

፮. ከአጥቢያው ሰበካ ጉባኤ ውጭ ሰእለ አድህኖ ይዘው ጥላ ዘቅዝቀው ምንጣፍ አንጥፈውከፈ.ቃድ ውጭ ገንዘብ የሚሰበስቡትን ይቆጣጠራል ፤

## <u>ክፍል ስምንት</u>

## <u>ልዩ ልዩ ድንጋጌዎች</u>

### <u>አንቀጽ ፴፬</u>

### <u>ደንቡ የሚጸናበት ጊዜ</u>

ይህ ደንብ በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ከጸደቀበት ከጥቅምት ፳፻፲፫ ዓ.ም ጀምሮ የጸና ይሆናል፡፡

### <u>አንቀጽ ፴፫</u>

### <u>ደንቡን ስለማሻሻል</u>

ይህን ደንብ ማሻሻል ሲያስፈልግ ሀገረ ስብከቱ የሚሻሻልበትን ምክንያት አጥንቶ በጠቅላይ ቤተክሕነት በኩል ለቋሚ ሲኖዶስ በማቅረብ ሲታመንበት በቅዱስ ሲኖዶስ ምልዓተ ጉባኤ ሊሻሻል ይችላል፡፡

ጥቅምት ፳፻፲፫ ዓ/ም

አዲስ አበባ ኢትዮጵያ